# የሚለኒየም አዳራሽ አጠቃቅምና አይን ያወጣ ተስፋፊነት

ዘውዲቱ የማነ

2019-08-06

ይህ የሚለኒየም አዳራሽ የኢትዮጵያን ህዝብ ደፍጥጠውና ተጭነው በሞጋሳ ኦሮሞ ለማድረግ ለተነሱ ፅንፈኞች ብቻ መፈቀዱ የዶ/ር አብይ አህመድን የአድሎ አስተዳደርና የታከለ ኡማን ማን አለብኝነት ማሳያ ነው። ለእስክንድር ነጋ መፈናፈኛ ያሳጣች አዲስ አበባ የከተማዋን ነዋሪ በጠራራ ፀሀይ አፈናቅላ በዚህ ክረምት በሺ የሚቆጠሩ አባወራዎችን ቤት አልባ አድርጋ በርካታ ህፃናትን ያለመጠለያ ያስቀረች አዲስ አበባ ከተማ በህጋዊ መንገድ ተደራጅቶ ፈቃድ ያለው የፓለቲካ ድርጅት አብን ስብሰባ እንዳያካሂድ በተከለከለው የሚለኒየም አዳራሽ፣ በጫት የደነዘዘውና ሲመረቅን ሁሉ ነገር የኦሮሞ የሚመስለው ቀማኛ እዝቄል ጋቢሳ ቢጤዎቹን ሰብስቦ የተለመደውን ከልብ ወለድ የመንጨ ኬኛ ትርክቱንና የማጋጨት ቅስቀሳውን እንዲሰራ ተፈቀደለት። እንደዚህ አይነቱ አይን ያወጣ በአድልኦ ላይ የተገነባ ተስፋፊነት "የብሄር እኩልነት" ይባልልኛል!

እዝቄል በሚለንየም አዳራሽ የወሎ ሰው ሳያይና ሳይሰማ የእሱን ቢጤ ተስፋፊዎች ብቻ ሰብስቦ በማናለብኝነት "ወሎ ኩሽ ነው፣ ኦሮሞ ነው፣ በወሎ በኩል አድርገን" ቀጣዩን አካባቢ በጎሳ እናመሳቅላነን እያለ ሲዘባርቅ በመንግስት ተብየው ይሁንታ ነው።

ለመሆኑ አዴፓ ተብየው በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እያለ ነው? ያው እንደተለመደው በ 27 አመት ለወያኔ ባደረበት ሎሌነት ለአዴፓም የቆመ ይመስላል። አዴፓ ከህዝብ ወገን ቢቆም እሰየው ነው። ያን የማያደርግ ከሆነም ህዝቡ ለነፃነቱ የመቆም ግዴታ አለበት። ስለዚህ ወሎ ኬኛ ብሎ አታሞ የሚመታ ሁሉ ሊያውቀው የሚገባው እንኳን ወሎ የከሚሴ ወረዳም ሙሉ በሙሉ የእናንተ አይደለምና ተረጋጉ። በስልጣናችሁ ተመክታችሁ ወሎን ለመጨፍለቅ ካሰባችሁም ተሳስታችኋል። ምክንያቱም ቤተ አማራ/ወሎ እኛ ልጆቿ በህይወት እያለን መቸም የኦሮሞ አትሆንም። አባቶቻችን



”የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበጅ
የአውሬ መውለጃ ይሆናል እንጅ”

ይሉ ነበርና ያ ቀን የደረሰ ይመስላል።